# የሰቆጣ ወረዳ አለባበስና አጊያጌጥ ለውጥና ቀጣይነት

በአፀደ ተፈራ

## አኀጽሮተ-ጽሑፍ

የዚህ ጥናት አላማ በቁሳዊ ባህል ስር የሚጠቀሰውን የሰቆጣ ወረዳን አለባበስና አጊያጌጥ ለውጥና ቀጣይነት መግለጽ ነው፡፡ ጥናቴን በሰቆጣ ወረዳ ላይ እንዳከናወን ያነሳሳኝ ምክንያትም በወረዳው አለባበስና አጊያጌጥ ላይ የተጠና ጥናት ባለመኖሩና በሉላዊነትና ‹‹በዘመናዊነት›› ምክንያት ሀገረሰባዊ አለባበሱና አጊያጌጡ እየቀነሰና በሌሎች ዘመናዊ አልባሳትና አጊያጌጥ እየተተካ በመሄዱ፣ የማህበረሰቡ መገለጫነት ሊጠፋ ስለሚችል እንዲሰነድ ለማድረግ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለግሉትም ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና ሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡ መረጃው የተሰበሰበው በመስክ ጉዞ ነው፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው ባህላዊ አለባበሱና አጊያጌጡ ባሁኑ ጊዜ ከሞላ ጎደል የሚታየው በገጠር አካባቢ እንደሆነ ነው፤ ወደ ከተማ አካባቢ ግን ለውጡ ጎልቶ ይታያል፡፡ ስለሆነም ባህላዊ አለባበሱና አጊያጌጡ ገጽታውን ሳይለቅ እንዲቀጥል ማህበረሰቡና የሚመለከታቸውው አካላት ለወጣቶች ማስተማርና ጠቀሜታውን መግለጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡

*ቁልፍ ቃላት- ቁሳዊ ባህል፣ አልባሳት፣ አጊያጌጥ፣ ለውጥና ቀጣይነት*

### የጥናት አካባቢው ዳራዊ መግለጫ

የሰቆጣ ወረዳ ከዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ስር ከሚገኙት ሰባት ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር የሚገኘው በአማራ ክልል ሰሜናዊ ጫፍ ሲሆን፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ከትግራይ ክልል፣ በደቡብ ከሰሜን ወሎ፣ በምእራብ ከሰሜንና ከደቡብ ጎንደር ይዋሰናል። በማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (2003 ዓ.ም[1]፣ 24) መረጃ መሰረት፣ የዋግ ኽምራ አስተዳደር ዞን የመሬት ስፋት 9039.04 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ዞኑ በስድስት ወረዳዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር ተከፍሏል። እነዚህም ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር፣ ሰቆጣ፣ ድሃና፣ ስሃላ ሰየምት፣ አብርገሌ፣ ጋዝጊብላ፣ እና ዝቋላ ወረዳዎች ናቸው። እንደ ኤ.አ 2007 በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የብሄረሰብ አስተዳደሩ የህዝብ ብዛት 426,213 ነው።

የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዋና ከተማ ስትሆን፣ ከአዲስ አበባ ሰባት መቶ ሃያ ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህር ዳር አምስት መቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር፣ ከላሊበላ እና ከመቀሌ ደግሞ አንድ መቶ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።ይህች ከተማ ጥንታዊ ከሚባሉት

ከተማዎች መካከል ትጠቀሳለች። ይህንንም (Pankhurst,1982:125) ሲገልጹ፣ ሰቆጣ፣ የዋግ ዋና ከተማ፣ በዘር ሀረግ እየተወራረሱ የሚገዙት የዋግ ሹሞች መቀመጫ ስትሆን፣ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ታዋቂ ከነበሩት ከተማዎች ውስጥ አንዷ ናት ብለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በሰቆጣ ወረዳ ነው፡፡

**የጥናቱ ዓላማ**

የዚህ ጥናት አቢይና ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አቢይ ዓላማ**

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የሰቆጣ ወረዳን አለባበስና አጊያጌጥ ለውጥና ቀጣይነት መግለጽና እንዲሰነድ ማድረግ ሲሆን፣ በወረዳው የወንዶችና የሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ ምን እንደሚመስል እንዲሁም ለውጥና ቀጣይነቱ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በዝርዝር ዓላማነት የተቀመጡ ናቸው፡፡

**ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች**

1.በሰቆጣ ወረዳ የወንዶች አለባበስና አጊያጌጥ ምን ይመስላል?

2. በሰቆጣ ወረዳ የሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ ምን ይመስላል?

3.በሰቆጣ ወረዳ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጌጥ ቀጣይነት እንዴት ይገለጻል?

4. በሰቆጣ ወረዳ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጌጥ ለውጥ ምን ይመስላል?

**የጥናቱ ጠቀሜታ**

የዚህ ጥናት ጠቀሜታ በብሄረሰብ አስተዳደሩ የሰቆጣ ወረዳ አለባበስና የአጊያጌጥ እንዲሰነድና በሌሎችም እንዲታወቅ ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ ሆኖ ማገልግል ነው፡፡

**የጥናቱ ወሰን**

በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ሰባት ወረዳዎች ሲኖሩ ይህ ጥናት የተካሄደው ግን በሰቆጣ ወረዳ ላይ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ሌላዎቹ አምስት የገጠር ወረዳዎች መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ባለመሆናቸውና ረጂም ጊዜ የሚጠይቁ በመሆናቸው፣ የሰቆጣ ከተማ አለባበስና አጊያጌጥ ደግሞ በአብዛኛው ተለውጦ የሚታይ ስለሆነ ይህ ጥናት አልተመለከታቸውም፤ ይሁን እንጂ የሰቆጣ ወረዳ አለባበስና አጊያጌጥ ከሌላዎቹ አምስት የገጠር ወረዳዎች የጎላ ልዩነት አይኖረውም ፤ እንዲያውም ወረዳው ከአራቱ ጋር ተዋስኖ ስለሚገኝ ሊወክላቸው ይችላል በሚል ነው፡፡

**የአጠናን ዘዴ**

በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረገው ዓይነታዊ (Qualitative) የጥናት ዘዴ ሲሆን፣ መረጃው የተሰበሰበውም ከቀዳማይ (Primary) እና ከካልዓይ (Secondary) ምንጮች ነው፡፡ ቀዳማይ መረጃ የተሰበሰበው አለባበስንና አጊያጌጥን በመመልከት ሲሆን፣ ካልዓይ ምንጮች ደግሞ የተለያዩ ጽሑፋዊ መረጃዎች ናቸው፡፡

**የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች**

ባጠቃላይ ለዚህ ጥናት ያገለገለውን መረጃ ለመሰብሰብ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግሎት ላይ የዋሉት፣ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና ሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡

**የፎክሎር ምንነትና ዘውጎች (አይነቶች)**

አለባበስና አጊያጌጥ ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች መካከል በቁሳዊ ባህል ስር የሚጠቀስ ነው፡፡ ፎክሎር ማለት የአንድ ማህበረሰብ፣ ባህል፣ እምነት፣ ስርዓት አምልኮት አመጋገብ እና ልማድ ወዘተ የሚገልፅበት ዘርፍ ነው፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቡ በባህልም ሆነ በዘልማድ የሚተገበረው የሠዎች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ መለያ ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት ፈቃደ 1991፣1) Dorson, 1972. ጠቅሶ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ዛሬ "Foklore`` (ፎክሎር) የሚለውን ቃል የቋንቋው ተናጋሪዎች በእለት ተእለት ውይይት ውስጥ በተለያየ ፍች ይገለገልበታል፡፡ ቃሉ ፊደል ላልቆጠረው እና ለቆ ጠረው ጭምር በተለምደው አነጋገር (ላልተማረው እና ለተማረው የሚባለውን ለማለት) አከራካሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ቃሉ ውሸትን፣ ሳንካን፣ ልቅ ህልምን (fantast) ፣ ነገር ማዛባትን (Distorition) የመሳሰሉ ሀሳቦችን በሠዎች አእምሮ ውስጥ ይጠና ነበር፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ፎክሎር የሚለው ቃል ሰዎች በእለት ተእለት ኑሮአቸው ውስጥ ወይም ስራ ላይ የተለያየ ትርጓሜ እንደሚሰጡት እና እንዲሁም በትምህርት አለም ለተሠማሩት እና ላልተሠማሩት አወዛጋቢ ጉዳይ መሆኑን እና ቃሉ በሙያው መስክ ለተሠማሩት ሁሉ መጠሪያ መሆኑን መግለጻቸውን ነው፡፡ ፎክሎር ማለት የተለያዩ እምቶችን፣ ልማዶችን እና ባህሉን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለህዝብ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡

ቃሉ (ፎክሎር) ለጥናት መስኩ እና መስኩ ለሚያጠናቸው ነገሮችም በመጠሪያነት ያገለግል ነበር። ይህን ችግር ለመቅረፍ ለመስኩ ፎክሎርስቲክስ፣ ለሚጠናው ነገር ደግሞ፣ ፎክሎር የሚል መጠሪያ ተሰጠ ( Dundes፣1965፣3፤ Dorson፣1972፣5)። ፎክሎር ከሚያካትታቸው ውስጥ የተወሰኑትን (ስልሳ ያህሎቹን) ደንደስ ዘርዝሯቸዋል።(1965፣3) Maria Leach ባደተችው መጽሐፍ ቅጽ አንድ ላይ ደግሞ፣ ፎክሎር በሃያ አንድ የአሜሪካ ፎክሎረኞች አማካይነት የተለያየ

ፍች ተሰጥቶት ይገኛል (1950፤398-403)። የብሪታኒካ አውደ ጥበብ (1993፤ቅጽ፤19፤308) እና Simes and Stiphens (2005፤12) ደግሞ፣ ፎክሎር፣ ስነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል እና ልማድና ክብረ በዓላት ተብሎ በሦስት ቅርፆች ሊከፈል እንደሚችል አስፍረዋል። እንዲሁም Wilson (1986፣ 228)፣ ፎክሎርን በሶስት ከፍሎ እንደሚከተለው አስፍሯል። ሰዎች በቃላት የሚገልጿቸው፣ ቃላዊ ሎር (Verbal art)፣ ሰዎች በእጅ የሚሰሯቸው ቁሳዊ ሎር( Material lore)፣ ሰዎች በድርጊት የሚፈጽሟቸው ልማዳዊ ሎር (customery lore)።

በAlan Dundes ሆነ በሃያ አንዱ የአሜሪካ ፎክሎረኞች የተዘረዘሩትን ዶርሰን በአራት የጥናት ዘርፎች መድቧቸዋል። እነዚህም ስነ ቃል (Oral folklore)፣ ሀገረ-ሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk arts ) ሀገረ-ሰባዊ ልማድ (Social folk customs) እና ቁሳዊ ባህል (Material culture) (ፈ.ቃደ፤1991፣ ዶርሰንን ጠቅሶ፣ Dorson,1972:2) በDorsonም ሆነ በሌላዎቹ የፎክሎር አከፋፈል ከሚካተቱት ውስጥ አንዱ ቁሳዊ ባህል ነው።

እንደ ሰለሞን (2007፤249) በቁሳዊ ባህል ስር የሚካተቱ ነገሮች፣ እነዚህ ነገሮች ከምን እንደሚሰሩና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚተላለፉ ሲገልጽ፣ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ስርዓት ጀምሮ በባህላዊ መንገድ ድንጋይ ጠርቦ፣እንጨት አለስልሶ፣ ጭቃ አቡክቶ፣ ብረት አቅልጦ፣ ቆዳ አልፍቶ፣ ጥጥ ፈትሎ እንዲሁም ከተለያዩ የእጽዋት ቅርፊቶችና ስራስሮች ቀለም አዘጋጅቶ የራሱን ጥበብ መሰረት በማድረግ የሚሰራቸው ልብሶች፣ ጫማዎች፣ ጌጣጌጦች፣ ቤቶች፣ ድልድዮች ወዘተ.ናቸው፡፡

ባህላዊ ቁሶች የሚገለገልባቸውና የሚሰራቸው የሕብረተሰብ ክፍል መገለጫ ሊሆኑ እንደሚችሉ (Henery Glassie፤1968፤10ን በመጥቀስ ሰለሞን (2007፤248) እንደሚከተለው አስፍሯል፤

> እነዚህ ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ እምነት፣ ሃይማኖት፣ ባህል ወዘተ.መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የዘመን ተሞክሮ አሻራዎች የሚያሳዩ ጥበባዊ ውጤቶች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡም የቁሳዊ ባህሎችን ዕውቀትና የአሰራር ክህሎት ቁሶቹ ሲሰሩ በማየት፣ በማስታወስና በመስራት ከትውልድ ወደ ትውልድ ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ያስተላልፋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቁሳዊ ባህል ሌሎች ነገሮችን ሊገልጽ እንደሚችል በሚከተለው መልክ ቀርቧል፤

> ቁሳዊ ባህል ስንል በስሜት ህዋሶቻችን ከምናስተውላቸው ተጨባጭ ቁሶች በተጨማሪ ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚገለጹ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቡናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮችን አጠቃሎ የሚይዝ ሰፊ ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ ቁሳዊ ባህሎች በዕለት ዕለት የሕይወት እንቅስቃሴያችን ወቅት ከምንጠቀምባቸው መሰረታዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ የእኛን ሀሳብ፣ እምነት፣ ሀይማኖት፣ አኗኗር፣ አስተዳደግ፣ ጾታ፣ ያለንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ወዘተ.ማሳያዎችና የማንነታችን መለያ ማህተም የሰፈረባቸው ቁሶች ናቸው፡፡ (ሰለሞን፤2007፤249-250)፡፡

ቁሳዊ ባህል የማህበረሰቡን ሁኔታ ሊገልጹ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ጉለሹ የአንድ ህዝብ ቀደምት ባህልና ታሪክ በመንፈሳዊ እሴቱ እንደሚገለጸው ሁሉ በቁሳዊ ባህሉም ሊገለጽ ይችላል ያለው (1987፣8)፡፡በቁሳዊ ባህል ስር ከሚመደቡት ነገሮች መካከል አንዱ ንቅሳት ነው፤ንቅሳት በማጌጫነት ብቻ ሳይሆን ለሌላ ተግባር ከዋለ ለማጌጫነት በመዋሉ በቁሳዊ ባህል መፈረጁ ቀርቶ በሌላ የፎክሎር ዘውግ ሊመደብ እንደሚችል ሲገለጽ፣

> ከሴቶች ማጋጌጫ ንቅሳቱ በሀገረሰባዊ ስንክን ዘርፍ ውስጥ ሊመደብ የሚችለው የንቅሳቱ ተቀዳሚ ዓላማ ለውበት ወይም ለደስታ (for the sake of pleasure) ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የንቅሳቱ ተቀዳሚ ዓላማ ከቡዳ ለመከላከል ከሆነ በሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ እንጂ በሀገረሰባዊ ስንክን የፎክሎር ዘርፍ ውስጥ አንመድበውም፡፡ (ሰለሞን.2007፣255)

ቁሳዊ ባህል ባለው የጥናት ዘርፍ ውስጥ አምስት አበይት ነገሮችን Dorson (1972፣2) አካትቷል። እነዚህም ሀገረሰባዊ እጅ ስራን፣ (folk crafts)፣ ሀገረሰባዊ ስእልን( folk art) ሀገረሰባዊ ምህንድስናን (folk architecture) ሀገረሰባዊ ልብስን( folk costume) እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራርን (folk cookery) (ፈቃደ፣1991፣ Dorsonንን ጠቅሶ፣

አለባበስና አጊያጌጥ ከማህበረሰቡ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለውጥና ቀጣይነት ይታይበታል፡፡

**የሰቆጣ ወረዳ ህዝብ አለባበስና አጊያጌጥ**

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አለባበስና አጊያጌጥ በፎክሎር በቁሳዊ ባህል ስር ይመደባል፤ ከዚህ አንጻር የሰቆጣ ከተማ የወንዶችና የሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ ምን ይመስላል ለሚለው ጥያቄ ምላሹን እንመለከታለን፡፡

**የወንዶች አለባበስና አጊያጌጥ**

የወንዶችን አለባበስ የልጆች፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። ወንዶች ልጆች የሚለብሱት **ኪታ** ነው። ይህም ከተለያዩ የልብስ አይነቶች የተሰፋ ሆኖ የኪሱ ጫፍ በጥልፍ ወይም በዛጎልና ድባ ይዋባል። ጸጉራቸውንም ከመሃል ቁንጮ አስቀርተው ሌላውን ይላጫሉ፡፡

ወጣት ወንዶች ደግሞ ቁምጣና እጅጌው አጭር ሆኖ በጀርባና በፊት ለፊት በልብስ ቁልፍ (**መከተሪያ**) እና በዛጎል ያጌጠ፣ ሸሚዝ **ኳርቶ**[2]ይለብሳሉ፤ በቁምጣቸው ላይ ለውበትና እሾህ ሲወጋቸው ለማውጣት የሚጠቀሙባትን ወረንጦም ያንጠለጥላሉ። በስራ ጊዜ በአካባቢው የእደ

[2] ሶራ የተሰኘውን ዘፈን የሚያቀነቅነውም ሆነ የሚቀበሉት ወንዶች፣ ይህንን በመልበሳቸው ፣ በአሁኑ ጊዜ ይህ ልብስ ሶራ ተብሎ እየተጠራ ነው፡፡

ጥበብ ባለሙያዎች ከጎማ የተሰራ ጥልፍልፍ ጫማ በአካባቢው አጠራር **እንደርታ** ወይም **ባራባሶ**፣ በሌላ ጊዜ ግን በፋብሪካ የተሰራ ዘመናዊ ጫማ ያደርጋሉ። ጸጉራቸውንም ጎፈሬ ያደርጋሉ። አንዳንዶችም ለጌጥ ጥርሳቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም ጉራማይሌ ይነቀሳሉ። ክንዳቸው ላይም የመስቀል ቅርጽ ይነቀሳሉ፣ ክንዳቸውንም የከብ ቅርጽ ያለው አድርገው በእሳት በማቃጠል (**በምስር ቂጣ**[3]) የጀግንነት ምልክት ተብሎ የሚገመት ጠባሳ ያደርጋሉ።ቃለመጠይቅ ያደረግሁለት ወጣት እንደገለጸው እሳቱ ቢያቃጥልም፣ ከጓደኛ ላለማነስና ላለመለየት ምስር ቂጣ ይደረጋል፡፡



ጸጉራቸውን ቁንጮ የተላጩና ኪታ የለበሱ ልጆች ቁርንጮ4 ላይ ተቀምጠው (ፎቶ በዋግ ኸምራ ዞን ባቱ[5])

[3] በወንዶች ክንድ ላይ የሚታይ ሰፊ ጠባሳ ነው፡፡
[4] ከለፋ ቆዳ የተሰራች፣ ለመመገቢያነት፣ለልብስነትና ለመቀመጫነት የምታገለግል ናት፡፡
[5] ባህልና ቱሪዝም



ኳርቶ የለበሱ ወጣቶች

የአባቶች አለባበስ ደግሞ በክትና በዘወትር የሚከፈል ነው። ዘወትር የሚለብሱት በተለይም በእርሻ ስራ ወቅት ቆሸሽ ያለ ቁምጣና እጅጌው አጭር የሆነ ሸሚዝ ነው፤ ዝናብ ሲመጣ ለመከላከል ያስችላቸው ዘንድ ትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት ደግሞ በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያ ከቆዳ የተሰራ **ቁርንጮ** (በኽምጣኛ በልባል)ነው። የክት ልብሳቸው ነጭ ባት ተሁለት[6] ሱሪ ወይም ሌላ ሱሪና ሳሪያን ኮት በቀጭኑ ተፈትሎ የተሰራ ጋቢ ከጭራ ጋር ነው። ጸጉራቸውንም እንደ ወጣቶቹ በጣም አያጎፍሩትም፤ ያሳጥሩታል፤ በእድሜ የገፉት ግን ጸጉራቸውን አያሳድጉም፤ ይላጩታል።

[6] ይህ የሱሪ አይነት የሁለቱ ባቶች አሰፋፍ ጠባብ ሆኖ የሚሰፋ ነው፡፡



የአባቶች አለባበስ[7]

**የሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ**

የሴቶችን አለባበስም የልጆች፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። ሴቶች ልጆች ያልተሸበሸበ ቀሚስ (**ጥብቆ**) ይለብሳሉ። ይህም በአብዛኛው ከጥጥ የተሰራና በመቀነት የሚታጠቁት ነው። ጸጉራቸውንም ሌላውን ተላጭተው አራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ጸጉር መሃል ላይ ብቻ ትተው በመሰራት **በሰለላ** ጀምረው፣ ሁለት ዙር ጋሜና ቁንጮ ይሰራሉ።

[7] ይህ አለባበስ የአዘቦት አለባበስ ነው፡፡



*ጋሜና ቁንጮ የተሰራችና ቃቂዳ[8] ያሰረች ወጣት[9]*

ወጣቶቹ ደግሞ ቀሚስ በመቀነት ታጥቀው ይለብሳሉ፡፡ እስከሚወልዱ ድረስ ሰፋ ያለ ጋሜና ቁንጮ ይሰራሉ፤ ደጋግመው ከወለዱ በኋላም ሳዱላ (**ቅርድድ**) ይሰራሉ፤ ይህም ከመሀል ጸጉራቸውን በክብ ቅርጽ በመላጨት ሌላውን ሹሩባ የሚሰሩት ነው። ትልቅ ሴት ወይም እናት ሲሆኑ ደግሞ ጸጉራቸውን ሙሉ በሙሉ ሳይላጩ ያሳድጉና ሹርባ ይሰራሉ፤ የጎደለውን ድፍን ያደርጋሉ። በአሁኑ ጊዜ ግን ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ተያይዞ ሕጻናትም ሆኑ ወጣቶች ፀጉራቸውን ድፍን እያደረጉ ነው።

ይህም ቀደም ሲል የእድሜ ልዩነት መግለጫና መለያ የነበረው የጸጉር አስተዳደግና አለጫጨት ሙሉ በሙሉ ባይጠፋም፣ እየቀነሰ መምጣቱን ያመለክታል።

[8] ከሳር የሚሰራ የእራስ ጌጥ

[9] የወጣቷ አለባበስ የአዘቦት ቀንም ነው፡፡

ሴቶች ሹሩባቸውን በተለያየ አይነት ይሰራሉ፤ መደረቢያ የሌለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ (**አሻሞ**)፣ መደረቢያ ያለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ (**አልባሶ**)፣ ገፅታው ተገልብጦ የሚሰራ ሹሩባ (**ግልብጭ**)፣ ገፅታው ሳይገለበጥ የሚሰራ ሹሩባ (**ግጫ**)፣ በጣም ወፍራም ሹሩባ፣ (**ጉንጉን**)፣ ጫፉ ወይም ዱርላው ተሰብስቦ የሚሰራ ሹሩባ (ድርማሞ) እና ወፍራምና ቀጭን ተደባልቆ የሚሰራ ሹሩባና በቅርብ የሚታይ **ጎበዝና ቆንጆ** ይሰራሉ፤ በተለይ ወጣቶቹ በሹርባቸው መሀል ላይ በጌጥነት ወለባቸውን ይሰካሉ። በቆላው አካባቢ ደግሞ **ቃቂዳ** የምትባል ከሳር የምትሰራ የጸጉር ጌጥ ያስራሉ፡፡

እነዚህ የጸጉር አሰራር አይነቶች ወቅትንና ሴቷ የምትገኝበትን ሁኔታ መሰረት ያደርጋሉ። አሻሞና ጉንጉን ለአጣዳፊ ጊዜና በሀዘን ወቅት የሚሰሯቸው ናቸው፤ድርማሞ ደግሞ ሴትየዋ በእድሜ በመግፋቷ በዱርላዋ ላለማጌጥ ስትፈልግና የሀዘን ጊዜዋን ወደ ማጠናቀቅ ደረጃ ላይ ስትደርስ የምትሰራው ነው። አልባሶ በማንኛውም ጊዜ የሚሰሩት ሲሆን፣ ግልብጭና ግጫ ግን ሴቶች ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ተውበው መታየት በሚገባቸው፣ በክብረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በክርስትና ወዘተ.የሚሰሯቸው ናቸው። እነዚህ የጸጉር አሰራር አይነቶች ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በተለይ ጸጉራቸው ብዙ የሆነ ሴቶች ቀኑን ሙሉ ሲሰሩ የሚውሉበትም ጊዜ አለ፡፡ ለነዚህ ነው በአካባቢው፣

አንድ ቀን ተሰርቶ አያልቅም እራሿ፣[10]
ላምባዲና ይገፔ ልቁም ከትራሿ፡፡

የሚል የፍቅር ቃል ግጥም የሚገጠምላቸው፡፡

አለባበስን በሚመለከት ወጣቶቹም ሆኑ እናቶች ከጥጥ ፈትል የተሰራ ወይም ከዝሃ ብቻ የተሰራ (**እሱ በእሱ**) ወይም ከፈትልና ከዝሃ ተደባልቆ የሚሰራ (**ጀበርባሬ**) ይለብሳሉ፤ ቀሚሳቸውንም ሆነ ኩታቸውን የተለያየ ቀለም ባላቸው የክር አይነቶች (**እዳይቶች**) ያስውቡታል። በአካባቢው ተዘውትረው የሚመረጡት የክር ዓይነቶችም አረንጓዴ (**ቅጠልያ**) ወይም (**ወንዝ አይፈሬ**)[11]እና ሰማያዊ (**ድባ ዓይነት**) ናቸው። ቀሚሳቸውንም በጥልፍ ያሳምሩታል፤ ጥልፉ የቀሚሱ ግማሽ ብቻ የተጠለፈ (**ፍቅር ቁምጥ**) ወይም ሙሉ ጥልፍ ሊሆን ይችላል። በቀሚሱ ጥልፍ ላይ የሚያያዝ መልጎምም ያደርጋሉ፡፡ መልጎም ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራ ክብ ቅርጽ ያለው ጌጥ ነው፡፡ የሚታጠቁት መቀነትም ተራ ወይም እስከ ስድስት ዓይነት በሚደርሱ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክር የተዋበ፣ ሰፊ ጥለት ያለውና ዋጋው እጅግ በጣም ውድ የሆነ (**ቃንጃ መትር**)[12]ሊሆን ይችላል። ነጠላም ይደርባሉ።

አጊያጌጣቸውን በሚመለከት እንደ እድሜ ደረጃቸው ከእራሳቸው እስከ እግራቸው ከተለያዩ ነገሮች የተሰሩ ጌጣጌጦችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህም መካከል፣ ቀራንዮ መስቀል (ትንሽና ትልቁን)

---

[10] ጸጉሯ ለማለት ነው፡፡
[11] አረንጓዴ  ለማለት ነው፡፡
[12] ከዋጋው ውድነት የተነሳ ከአንድ በሬ ዋጋ  ጋር እኩል  ነው ለማለት ነው፡፡

በአንገታቸው ያስራሉ፤ ድሪና ድንብል ቀለበትም የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮችና ለስላሳ በሆነ ጥቁር ክር (**ካሉስ**) በሚባለው ክር ታስሮ መዋቢያ ነው። ጣታቸው ላይም ቀለበት ያደርጋሉ። ክንዳቸው ላይም ባለ ማፈኛና ማፈኛ የሌለው ሁለት ዓይነት አምባር (ድኮት) ያደርጋሉ። እግራቸው ላይም አልቦ ያስራሉ። በጣታቸውም ከብር፣ ከኒኬል ወይም ከመዳብ የሚሰራ ቀለበት፣ ደግሞ ከስንድድና ከ**አሽከት** (ቅጠሉ ትንንሽና የሚያጣብቅ የተክል) አይነት ፍሬ በክር ተደርድሮ ወይም ከሳር የሚሰራ የጌፕ አይነት (**ቃቂዳ**) ግንባራቸው ላይ ያስራሉ፣ በጆሯቸው ደግሞ በታችኛው ክፍል ቀለበት (**አላድ**) ወይም ጉትቻ፣ የላይኛው ጫፍ ደግሞ ሽንቆር ያደርጋሉ፡፡



ቃንጃ መትር መቀነት የታጠቀች ወጣት ( ፎቶ በዋግ በኽምራ ዞን ባቱ)



በአብዛኛዎቹ የልጃገረድ ጌጣጌጦች ያጌጠች ወጣት (ፎቶ በዋግ ኽምራ ዞን ባቱ)

ሌላው የሴቶች ማጌጫ ደግሞ ንቅሳት (**ውቅራት**) ነው። ግንባራቸውን፣ የአይኖቻቸውን ጎንና ጎን፣ አገጫቸውን፣ ጥርሶቻቸውንና በተለይ እናቶች ደግሞ፣ ከአንገታቸው ጀምሮ ወደታች እስከ ጡታቸው ጫፍ ድረስ ይነቀሳሉ (**ይወቀራሉ**)። የግንባራቸውንና የአገጫቸውን ንቅሳት ቅርጽ(ክብ ቅርጽና ከታች የመስቀል ቅርጽ ያለውን) በሚመለከት ከፍያለው (1992፣13)፣ ህዝቡ ከሚከተለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና መስፋፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለጽ በምስል አስደግፈው አቅርበዋል።

የጥርስና የአካል ንቅሳት በአካባቢው ለሴቶችም ለወንዶችም የሚያገለግል ነው፡፡

**የአለባበስና አጊያጌጥ ለውጥና ቀጣይነት**

ፎክሎር ከማህበረሰቡ ህልውና ጋር የተያያዘ ነው በዚህም ምክንያት በማህበረሰቡ ላይ የሚታዩ ለውጦች በፎክሎር ላይም ይንጸባረቃል፡፡ የምንገኝበት ዘመን የሉላዊነትና በበርካታ የመገናኛ ብዙኀን ተጠቃሚ የሆንበት ዘመን ነው፡፡ ከእነዚህም አንዱየኢንተርኔት ግንኙነት ነው፡፡ይህ ግንኙነት በአንድ አካባቢና ዘመን በሚገኝ የፎክሎር ዘውግ ላይ የሚያሳድረውን ለውጥ በሚመለከት Barre (1979,11) ሲገልጽ «ከኢንተርኔት ግንኙነትና ከውጭ ቋንቋ ትምህርት መስፋፋት ጋርተያይዞ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የፎክሎር ለውጥ ፈጣን ነው፡፡በዚህም ምክንያት

የፍች ለውጥ ከቦታ እና ከጊዜ አንጻር ያጋጥመዋል፡፡የለውጥ ሌላው ምክንያት ደግሞ የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች መስተጋብር መፈጠር ነው፡፡ይህንን አስመልክቶ (Viduka) ሲገልጽ የቁሳዊ ባህል ለውጥ ሊከሰት ከሚችልባቸው ምክንያቶች መካከል እንደ ስደትና የሰዎች ግንኙነት ነው (2012,5) ይላል፡፡

በዚህም ምክንያት እንደ ስልጣኔ እየተወሰደ ሀገረሰባዊ ባህላችን በምእራባውያኑ እየተተካ የራሳችንን ባህል እየተውን በእነሱ በመወረር ላይ እንገኛለን፡፡

የሰቆጣ ወረዳ አለባበስና አጊያጌጥ ሁኔታም ከዚህ ውጭ ሊሆን አልቻለም፤አልቻለምም፡፡ ቀደም ብለን የጠቀስናቸው አለባበሶችና አጊያጌጦች በዘመናዊ አለበዘበስና አጊያጌጥ እየተተካ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የወንዶች የጸጉር አቆራረጥ በከተማ አካባቢ የሚታየው አይነት እየሆነ መጥቷል፡፡ የሴቶች የተለያዩ የሹሩባ አሰራሮች በወጣቶች የሚዘወተር አይደለም፤ የጸጉር አለሜጨትና የሽሩባ አሰራርም የእድሜ መገለጫቸው በመቀነስ ላይ ይገኛል፡፡ የእናቶች ጥልፍ ቀሚስም በፋብሪካ ውጤት አልባሳት ተተክቷል፡፡

ለቀጣይነቱን እየታደገ ያለው ሃይማኖታዊ፣ ወቅታዊና ፖለቲካዊ ክብረ በዓላት ናቸው፡፡ እነዚህ ወቅቶች ማህበረሰቡ ባህላዊ አልባሳትን እንዲለብስ የሚያስገድዱ ናቸው፡፡ በዚህም አባቶች ሳሪያን ኮት፣ ወጣት ወንዶች ደግሞ ኳርቶ እንዲለብሱ፣ እናቶችም በተለያዩ ጥልፎች የተዋቡ ባህላዊ አልባሳትን እንዲለብሱና የተለያዩ የጸጉር አሰራሮችን በመሰራት በነባር ባህላዊ አጊያጌጦቻቸው እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው፡፡ ከእነሱም አልፎ በእንግድነት ወደ አካባቢው ለሚሄዱ የክብር እንግዶችም ለሴቶቹ የሴቶች ባህላዊ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን፣ ለወንዶች ደግሞ በእድሜ ለገፉት ሳሪያን ኮት፣ ለወጣት ወንዶች ደግሞ ኳርቶ ስጦታ እየተሰጠ ነው፡፡ ከከተማ ወደ አካባቢው የሚሄዱ ተወላጆችም ባህላዊ አልባሳቱን እየገዙ ይለብሳሉ፡፡ ለዚህ ነው ቃለመጠይቅ ያደረግሁላቸው የኳርቶ አሳማሪዎችና ሰፊዎች እንደገለጹት ገቢያቸው ከፍተኛ የሚሆነው በሃይማኖታዊ በክብረ-በዓላትና በፖለቲካዊ ክብረበዓላት በተለይም በየዓመቱ በሚካሄዱ አውደ ጥናቶች ነው ፡፡

**ማጠቃለያ**

የሰቆጣ ወረዳ አለባብስና አጊያጌጥ የማህበረሰቡን ደረጃ እና እድሜ የሚያመለክት ሲሆን በአብዛኛው በአካባቢው የእደ-ጥበብ ባለሙያ እና ከአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የሚሰራ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልክ የሚታየው ከመኪና መንገድ ራቅ ተብሎ ሲኬድና በክብረ በዓላት ወቅት ነው፡፡ በዚህ አለባበስስና አጊያጌጥ ተውበው የሚገኙት ደግሞ ከወጣቶች ይልቅ አባቶችና እናቶች ናቸው፤ ይህም የሚያመለክተው ወጣቱ በአካባቢው ባለሙያዎች ከተሰሩ ይልቅ በፋብሪካ በተሰሩ አለባበሶች እንደሚያጌጥ ነው፤ ይህ የሚያሳየን ባህላዊ አለባበሱ እየቀነሰ መምጣቱን ነው፡፡

**ምክረ ሀሳብ**

አለባበስና አጊያጌጥ የአንድ ማህበረሰብ ማንነት መገለጫ እና መኩሪያ ነው፡፡ የራስን እየተው የምእራባውያንን አለባበስና አጊያጌጥ መጠቀም በሂደት እኔነትን የሚያሳጣ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በሰቆጣና አካባቢዋ የተጀመረው በክብረበዓላትና በአውደጥናቶች የአካባቢውን አልባሳት መልበስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ከሚመለከታቸው የባህል ተቋማት ቀጣይነት ያለው ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

**ዋቢ መጻሕፍት**


ከፍያለው መራሒ (ቀሲስ)። (1992)። *የሴቶች መንፈሳዊ ህይወት*።አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፡፡ (2003) ፡፡ *ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት*፡፡

ጉለሹ በንኑ፣ነሐሴ (1987)‹‹በትንንሽ ኮረት ትልቅ ህድሞ››፣ማህቶት፣8፡፡

ፈቃደ አዘዘ። (1991)።*የሥነ ቃል መምሪያ*፤አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት።

Barre Toelken. (1979 ) *The Dynamics of Folklore*. Boston: Houghton Mifflin,

Dorson, Richard.M. (1972) '' Introduction: Concepts of Folklore and Folk life studies'' in Richard. M.Dorson, (ed.).*Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago and London: the University of Chicago Press.1-50. Retrieved from: *eprints.hud.ac.uk*

"Folk Arts." 1993. <u>The New Encyclopedia Britannica Macropedia</u>. Chicago: Encyclopedia Britannica Inc. Vol. 19, PP. 306-338.

Leach, Maria (ed.) (1950).*Standard Dictionary of Folklore Mythology, and Legend* Vol.II. NewYork: New York Publisher

Pankhurst, Richard. ( 1982.) <u>History of Ethiopian Towns from the Middle Ages to the Early Nineteenth Century</u>. Wiesbaden: Franz Steiner Verlag Gmbh.

Sims ,Martha C. & Martine Stephens. (2005).*Living Folklore: An introduction to the Study of people and their traditions.* Logan, Utah: Utah University Press.

Viduka J.Andrew (2012). *Material Culture*. Thailand: Published by UNESCO Bangkok.

Wilson, Wiliam, A. (1989).'' Documenting Folklore", in Elliott Oring, (ed.) *Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction.* Logan, Utah: Utah State University Press. 225-254.